በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሾች

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤት አባላት በወቅታዊና የመንግስት አቅጣጫ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። ዋና ዋናዎቹ ነጥቦችም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፤

**የህዝብን ሰላም እና ደህንነት ማረጋገጥ፡-** ወቅቱ ተቋም በማስቀጠል እና አገረ መንግስትን ማስቀጠል በመቻል ፈተና ውስጥ ያለንበት ነው፡፡ወደ ሴራ ፖለቲካ መሄድ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ያንን ማወቅ እና መከላከል የሚችል ተቋም እስኪገነባ ፈታኝ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን መስራት የሚጠይቅ ቢሆንም እየሆነ ያለው ሁሉ የሚታለፍ ፈተና ነው፡፡ የፌደራል መንግስት በህገ መንግስቱ በተቀመጠው መሰረት ወደ ክልሎች ሊገባ ይችላል ፡፡ዋና ተግባሩ ግን የአገርን ሉአላዊነት መጠበቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በውጭም በውስጥ አካላትም ብዙ ፈተናዎች ገጥመዋል፡፡ የከፋ ችግር ሳያደርሱ በደህንነት ሀይሉ የከሸፉ አሉ፡፡

**የኃይማኖት ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች ፡-**በአገራችን መስጊድም ቤተክርስቲያንም በፖሊስ መጠበቅ ልማድ አልነበረም፡፡ በጦርነት ጊዜ እንኳን የኃይማኖት ተቋማትን ማጥቃት ነውር ነበር፡፡ ስቴዲየም ውስጥ ፀብ ሁሌ የሚጠበቅ አልነበረም፡፡ ዩኒቨርሲቲ እየተጠበቀም ተማሪዎች እርስ በርስ ይገዳደላሉ፡፡ ይህ አዳዲስ ነውረኛ ልምምድ ነው፡፡ ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ሊፈፀምበት አይገባም፡፡እርስ በርስ ደግሞ ፀያፍ ነው፡፡ ይህ ነው እየሆነ ያለው፡፡

**የተማሪዎች እገታ ፡-** እገታውን ፈፅሜያለሁ ያለ የተደራጀ ኃይል የለም፡፡መረጃ ስናጣራ ተማሪ ያልሆኑም ተገኝተዋል፡፡ ታግቶም ይሁን ተደብቆ አልታገቱም የሚል መልስ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡በአንድም ስፍራ የሞተ የተጎዳ የለም፡፡ በግልፅ አግቻለሁ ያለ ሲጠፋ ማሰስ የግድ ይላል፡፡ተጎጂው ሁሉም ነው፡፡ እንዳሻን በመናገራችን ዜጎችን ችግር ውስጥ እንዳናስገባ ተጠንቅቀናል፡፡ ኮሚቴው ስራውን እየሰራ ነው፡፡ መረጃ ለምን አልተሰጠም ለሚለው ኦፐሬሽኑን መረዳት ይጠይቃል፡፡ ያልተደራጁ አጋቾች ከሆኑ ለልጆቹ ህይወት ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ደም እየተቃባን እንዳንሄድ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ሰው በማንነቱ ይታገታል ለሚለው ተማሪ ማንነት የለውም፡፡ሌላ አገር አልሄደም ይህንን ማጥቃት አሳፋሪ ነው፡፡

**በወለጋ እና ጉጂ አካባቢ፡-** በወለጋ የተለያዩ አካባቢዎች በመንግስት ፣በታጠቁ ኃይሎች እንዲሁም በባለሀብቶች ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ በምስራቅ ወለጋ አሁንም ብዙ ስራ የሚጠይቁ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ጥሩ የሚሆነው ችግሮችን በውይይት እና በሰላም መፍታት ነው፡፡ መከላከያ ቢገድል ወንድሞቹን ነው የሚገድለው፡፡ ይህ አያኮራም፡፡ ነገር ግን በአንድ አገር ሁለት የታጠቀ እና ሁለት መንግስት መኖር አይችልም፡፡ሊያውም ለዴሞክራሲ እጇን በከፈተች አገር ይህ ሊሆን አይገባም፡፡ በወለጋ አካባቢ መንግስትን ደካማ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት ነው ያለው፡፡ በአንድ በኩል ሰላም ማስከበር አልቻላችሁም በሌላ በኩል ወታደሩን አስወጡልን የሚል ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ አስተሳሰብ ነው ያለው፡፡ በዚህ መንገድ የሚሄድ ፖለቲካ በ1966 ዓ.ም የነበረ እንደሆን እንጂ በ2010ዓ.ም መሰረት የለውም ፡፡ በተለወጠ አገር ያልተለወጠ አስተሳሰብ ይዞ መጓዝ አሸናፊ አያደርግም፡፡ በነፃነት እና በዝግ መካከል ያለውን ስፍራ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ህግ እየጠፋ ዝም ማለት ዋጋ የለውም፡፡ወንወጀለኛን መሸፈን ተገቢ አይደለም፡፡ በደምቢ ዶሎ እና ጊምቢ ኔትወርክ ተቋርጦ ቆይቷል፡፡ ከኦፐሬሽን ጋር የተያያዘ ነው በቅርቡ ይለቀቃል፡፡

**ደቡብ ኦሞ ድንበር ግጭት፡-** አካባቢው ለኬንያ ይዋሰናል፡፡ በሁለቱም በኩል አርብቶአደሮች አሉ፡፡ ኑሯቸውን ለማሻሻል፣ ለከብቶች እንዲሁም ነዋሪው አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ እና የንግድ ማዕከላት ግንባታ ተጀምሯል፡፡ በኬንያ በኩል ይህ አልተሰራም ፡፡ የኬንያ አርብቶአደሮች እነዚህን አገልግሎቶች ፍለጋ ወደዚህ ስለሚመጡ ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡ የጋራ ድንበር ልማት እንዲኖር ከኬንያ መንግስት ጋር ተነጋግረንበታል፡፡

**የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ማዛወር፡-** ላለፉት 20 ዓመታት 287 ድርጅቶች በ49.2 ቢሊዮን ብር ወደ ግል ተዛውረዋል ፡፡ የፖለቲካ ለውጥ የሚያስብል ነገር የለውም፡፡ከለውጡ በኋላ አንድም ድርጅት አልተዛወረም፡፡ በፊት የተዛወሩት ላይ በቡድን እና በዘመድ የመሰሉ ችግሮች ስለነበሩ ያ እንዳይደገም ይህንን የሚመሩ ተቋማቱን እያጠናከርን ነው፡፡ እንደ ኢትዮ ቴሌኮም የመሰሉትን ከሆነ ከውጭ የብድር ጫና ስለነበረብን ሌላ ብድር ማግኘት ስለማንችል አዲስ ካፒታል አዳዲስ ዕውቀት ማግኘት ስለነበረብን አገሪቱም ወደኋላ እንዳትመለስ አዲስ ፖሊሲ ያስፈልግ ነበር፡፡ ልማት ማምጣት እንደምንችል በመታመኑ ዕዳ መቀነስ የብድር ጊዜ ማራዘም ችለናል፡፡

**ለአገር ውስጥ ባለሀብት የሚደረግ ድጋፍ፡-** የፋይናነስ ዘርፉን ብንወስድ ከለውጡ በፊት አንድ ባለሀብት በባንክ ካስቀመጠው 27 በመቶ ቦንድ እንዲገዛ ይገደድ ነበር፡፡ ለዚህም ወለድ አልነበረውም፡፡ ይህንን በማስቀረታችን ለብድርና ለወለድ ምጣኔ መቀነስ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ የግል ባንኮች የሊኩዲቲ እጥረት ሲያጋጥማቸው 14.5ቢሊየን ብር ፈሰስ ተደርጎላቸዋል፡፡በዚህ መጠን አይደረግም ነበር፡፡12 ገደማ አዳዲስ ባንኮች በሂደት ላይ ናቸው፡፡ ለውጭ ባለሀብቶች አልፈቀድንም የአገር ውስጦቹ እስኪጠናከሩ፡፡ ካለፈው ምርጥ ምርጡን ማስቀጠል ስለሆነ እንዳለ ቀጥለንበታል፡፡ በብዙ መልኩ ለግሉ ባለሀብት ድጋፍ እየተደረገ ነው፡፡

**ከልማት ይልቅ ለገፅታ ግንባታ፡-** ምክር ቤቱ ለገፅታ ግንባታ ምንም በጀት አላፀደቀም፡፡ ታዲያ ባልፀደቀ በጀት በምን እንደተሰራ ታስቦ ነው ለገፅታ ግንባታ ትኩረት ተሰጠ የሚባለው፡፡ እንደውም ይህ መንግስት ለገፅታ ግንባታ የተቋቋመውን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት አፍርሷል፡፡ የአመራር ችግሮችን በመፍታታችን ኢንዱስትሪያል ፓርኮች፣ ኢቲዮ ቴሌኮም፣ገቢ፣ ስኳር፣ መብራት፣ ህዳሴ ግድብ ሌሎቹም ብዙ ሊነገር የሚገባ ግን ያልተነገረ ውጤት ያስመዘገቡ ተቋማት ናቸው፡፡ የአዲስ አበባን በተመለከተ ባለሀብቶች እና አገራት ድጋፍ አድርገዋል፡፡እኛ የምናስበው ብልፅግና ቁጥር ብቻ የሚነገርበት አይደለም፡፡ ትልቅ ሀብት አለን ይህንን በአግባቡ ስንመራ ውጤት አግኝተናል፡፡ በቁንፅሉ ባንገነዘበው መልካም ነው፡፡

**የቻይና ኢንቨስተሮች ወደ ትግራይ፡-** የውጭ ዲፕሎማሲ የፌደራል ስልጣን ነው፡፡ በክልሉ በልማት በቱሪዝም እና በመሳሰሉት ግንኙነት ቢፈጠር መልካም ነገር ነው ፡፡ ነገር ግን ሆነ የተባለውን የደህንነት ሰዎች ስታገኙ ለምን እንደሆነ ጠይቁ፡፡

**ድንበርና ሰላም ኮሚሽን፡-** በአገራችን አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ እስኪደራጅ ሰዎች እስኪገኙ ጊዜ ይፈልጋል፡፡የትውውቅ ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል ም/ቤቱም ቢደግፋቸው መልካም ይሆናል፡፡

**የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዛት፡-**ፓርቲዎች ሀሳብ አቅራቢ ናቸው፡፡ ብልፅግና አርአያ ሆኖ ሰብሰብ እያለ ነው፡፡ነገር ግን የሚፎካከሩ ፓርቲዎች ዋና ትኩረታቸው መቃወም ከሆነ ውጤት አያመጡም፡፡መናገርና መስራት የተለያየ ነው፡፡ ልምድ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ለህዝብ አማራጭ በማቅረብ ነው አገር መምራት የሚቻለው፡፡ ብልፅግና ፓርቲ የተመረጠ ፓርቲ ፤ገዢ ፓርቲ ነው ፡፡ ምንም መደናገር አያስፈልግም፡፡ ምክር ቤት ውስጥ አብዛኛው መቀመጫ ስላለው መንግስት ነው፡፡

**ከትግራይ የተገፉ ባለስልጣናት፡-** አንድ ሚኒስትር ተነስተዋል፡፡ከአስር በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች አሉን፡፡ ድሮም በካቢኔ የነበራቸው ቁጥር እዛው ነው ያለው፡፡ የትግራይን ህዝብ ያገለለ መንግስት መፍጠር አይቻልም፡፡የትግራይ ህዝብ የመሳተፍ ሙሉ ብቃት አለው፡፡ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፈለገውን ካቢኔ የማደራጀት መብት አለው፤ እስከተመረጠ ድረስ፡፡ገዢው ፓርቲ ብልፅግና ነው፡፡ ከህወሀት ጋር ወደፊትም አብሮ ስለሚሰራ አልተገፋም አልተደረገም፡፡

**ምርጫ፡-** የምርጫ ቦርድ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ነው፡፡ የህግ ማሻሻያውን ለካቢኔ ሳይሆን ለምክር ቤት ነው ያቀረበው፡፡በህግ ጉዳይ እጃችንን አናስገባም፡፡ ህጉ የሚመለከተው ምክር ቤቱን ነው፡፡ የምርጫን ቀን በተመለከተ በህጉ መሰረት አንድ ወር ቀደም ብሎ መፈፀም ስላላበት ይህ ግድ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሰላም በዚህ ጊዜ ይረጋገጣል የሚያስብል መሰረት የለም፡፡ ምክር ቤቱ ሲያግዝ፣ ፓርቲዎች ሲተባበሩ፣ ዜጋው ጥበቃ ሲያደርግ ፣መንግስትም ካገዘ ይሳካል፡፡

**የደቡብ ክልል ጥያቄ፡-** በክልሉ የልማትና የፖለቲካ ጥያቄዎች አሉ፡፡ ክልል፣ዞን፣ ወረዳ ሲበዛ ደሞዝ ነው የሚጨምረው፡፡ይህንን ማመጣጠን ያስፈልጋል፡፡ምክክር ያስፈልጋል፡፡ክልል መሆን እና ራስን በራስ ማስተዳዳር አንድ እና ያው ከሆነ 80 ክልል ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ክልል ሳይሆኑ ማስተዳደር ይቻላል፡፡ህገ መንግስቱ ለማስፈፀም ሚያስችል ግልፅ ነገር አላስቀመጠም፡፡ ከህግ ሰዎች ጋር መምከር ያስፈልጋል፡፡ደቡብ ተጨፍልቆ አንድ ክልል ካልሆነ የሚል አቋም የለም፡፡ የጋራ ኮሚቴ አቋቁመናል ክልል ካበዛን የህዝቡን የልማት ጥያቄ እንጎዳለን፡፡ ምርጫ ቦርድ አቅም ያንሰዋል እየተባለ የክልልን ጉዳይ ያስፈፅም ማለትን ሰከን ብሎ ማሰብ ይጠይቃል፡፡

**በውጭ የተደበቁ ሀብቶች፡-** በውጭ የተደበቀ ሀብት አለ በቀላል መንገድ ማምጣት ይቻላል ወይ የሚለውን መመለስ ይገባል፡፡ ዐቃቤ ህግ ባቀረበው መንገድ መታየት አለበት አንዳንድ አገራት ከተስማሙ በኋላ ባንኮቻችንን ይጎዳል በሚል አገሪቱን ብንረዳ

ይሻላል ብለዋል፡፡ ኮሚቴ ተቋቁሟል የት ምን ያህል እንዳለ ማወቅ ቀላል ቢሆንም ማምጣት ግን ቀላል አይደለም፡፡ህገወጥ ዝውውውርን ለመቆጣጠር በተሰራ ስራ 14 ኪሎ ግራም ወርቅ እና 22.9 ሚሊዮን ዶላር ብሄራዊ ባንክ አለ፡፡ ሌላ መረጃ ካለ ጥቆማ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

**የቦንጋ ከተማ ውሃ፡-**በቅርቡ በተደረገ ውይይት ሆስፒታል እና ውሃን በተመለከተ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ኮሚቴ ተደራጅቷል፡፡ የሆስፒታሉ መልስ አግኝቷል፡፡ የውሃው ግን ሌሎችም 15 ተመሳሳይ ጥያቄ ያላቸው ከተሞች አሉ፡፡ የአብዛኞቹ ርክክብ ተካሂዷል፡፡ የቦንጋው የውሃ ማጣሪያው ችግር አለበት ምላሽ እንዲያገኝ እየተሰራ ነው፡፡

**የህዳሴ ግድብ ድርድር፡-** ድርድር ሳይቋጭ ጥቅሜን እስከብሬያለሁ አይባልም፡፡ የታችኛው ተፋሰስ አገራት መሰራት የለበትም ከሚለው ወደ አሞላሉ እና ወደሚሞላበት ጊዜ መጥቷል ድርድራቸው፡፡ እነ አሜሪካ እና የአለም ባንክ በጉዳዩ ላይ መግባታቸው በቀላሉ ለመግባባት ጥሩ ሆኗል፡፡ አሁንም ማየት የሚገባን ነገር ስላለ የምንወያይበት ይሆናል፡፡ ማንንም መጉዳት አንፈልግም መጎዳትም እንዲሁ፡፡ ጥያቄው በተፈጥሮ ውሃዬ ልጠቀም የሚል እና እንዳትጎዱን የሚል ተገቢ ጥያቄ ነው፡፡ ኢትዮጵያን በሚጎዳ ነገር ላይ የሚወስን መንግስት ኖሮን አያውቅም ወደፊትም አይኖርም፡፡

**የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ፡-** ብልፅግናችን የቁስ ብልፅግና ብቻ እንዲሆን አንፈልግም፡፡ፓርኮች ሲጠበቁ ለአካባቢው ህዝብ የሚጠቅሙ ከሆነ ፓርኩን እንደራሳቸው ይጠብቁታል ፡፡ እሳት ሲነሳ ተረባርበዋል፡፡ እንደሰሜን ፓርክ ለወጣቶች ስራ እየፈጠሩ ማልማት ያስፈልጋል፡፡እንደዛ ከሆነ ይጠበቃል፡፡

**የወጣቶች ስራ ፈጠራ፡-** ባለፉት 6 ወራት 1.2 ሚሊዮን ወጣት ስራ ተፈጥሮለታል፡፡በዓመት ያሰብነው 3 ሚሊዮን ነው፡፡ ከዚህ በኋላ 1.5 ሚሊዮን ወጣቶችን ስራ ማስጀመር ይጠበቅብናል ፡፡የስራ ፈጠራ ኮሚሽን ከውጭ 240 ሚሊዮን ዶላር አምጥቶ ለዚህ እየሰራ ነው፡፡ካለብን ድህነት አንጻር ብዙ ይጠበቅብናል ፡፡ የታክስ ስርዓቱን ከዚህ አንፃር ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ ውጤቱ የተሻለ ነው፡፡ በቅርብ ዓመታት ግን ሁሉንም ወጣት ስራ ማስያዝ እንችላለን አይባልም፡፡

**የነቀምት ጉሬ መንገድ፡-** *መንገዱ በጣም አስፈላጊ ነው በአለምባንክ ድጋፍ በአንድ የህንድ ኩባንያ የተጀመረ ቢሆንም እንደገና ጨረታ ወጥቶ ለአዲስ ኩባንያ ተላልፎ መሰራት ስላለበት ከፍተኛ ክትትል እየተደረገ ነው፡፡*

**አንበጣ፡-** በተደረገው ርብርብ ለመቆጣጠር ጥረት ተደርጓል፡፡ የግብርና ሚኒስቴር ከፍተኛ ስራ ሲሰራ ነበረ፡፡ ከሌላ ቦታ ሸሽቶ የመጣ በመሆኑ አገር ተደራጅቶ ካልተዋጋው በሚቀጥለው ምርት ዘመን ጉዳት ስለሚያመጣ እየተሰራበት ነው ፡፡ጉዳት ካጋጠመ የአደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**መረጃ መከልከል፡-** *መረጃ የመስጠት ባህል የለንም፡፡ ልምምዳችን ውስንነት አለበት፡፡ ስንቀበልም የመመዘንና የማጥራት ችግር አለ፡፡ የማሰራጫ መንገድም ውስንነት አለ፡፡በየመስሪያ ቤቱ ህዝብ ግንኙነት ባለሞያዎች አሉ፡፡ ስራቸውን መግለፅ አለባቸው፡፡*

**ጋዜጠኛ ታሰረ፡-** የኛን ሀሳብ የማይደግፉ ቢታሰሩ ተጨማሪ እስር ቤት ያስፈልገን ነበር፡፡ በየማህበራዊ ሚዲያው እንደፈለጉ የሚናገሩ ብዙ ናቸው፡፡ ጠዋት ጋዜጠኛ ከሰዓት ሌላ እየሆኑ ከሆነ ችግር አለ፡፡ብዙ የታሰረ ያለ አይመስለኝም፡፡ አልፎ አልፎ ይኖራል፡፡ ግን የተሻለ ዘመን ነው፡፡ ጋዜጠኞቹ ህግ አክብረው እስከሰሩ ድረስ ችግር የለም ፡፡ ሁሉ ነገር ፖለቲካ እና ፈጠራ ከሆነ ነው ችግሩ፡፡ ጃም የተደረጉ በመለቀቃቸው ብዙ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አለ፡፡ ህግን ተከትሎ በአግባቡ መረጃ መስጠት ያስፈልጋል፡ፕሬስ ሴክሬተሪ ማለት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ማለት አይደለም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ስራ ብቻ የሚዘግብ ነው፡፡ በጋራ የሚያሳውቁት መረጃ ሲኖር አብረው ይሰራሉ፡፡በየወረዳው ችግር ሲኖር አልተገለፀም የሚባለው ስህተት ነው፡፡ ወደፊት ፕሬስ ሴክሬተሪው እየተጠናከረ ይሄዳል፡፡

**አርብቶ አደር ልማት፡-** በሙብራት፣ በመስኖ በሌሎቹም የተሰሩ ስራዎች አሉ፡፡ በሰላም ሚኒስቴር እና በም/ጠ/ሚኒስትሩ በኩል ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል፤ ኑሮውን ለማሻሻል የሚረዱ፡፡ ከ 20 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በአፋር ፣ሶማሌ እና ሸንሌ እንዲሁም ሌሎች አካባቢዎች ለምቷል፡፡ የሰላም ሚኒስቴር 450 ሚሊዮን ዶላር ሰብስቦ አቅም ግንባታ ላይ እዚያ አካባቢ እየሰራ ነው፡፡ ከፖሊሲዎች ጋር በተገናኘ በቅርቡ የሚፀድቁ አሉ፡፡

//